# ገንዘብ ሚኒስቴር

## የቅድመ ግብር ክፍያ ሥርዓት አፈፃፀም
## መመሪያ ቁጥር 2/2011

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

ገንዘብ ሚኒስቴር

መጋቢት 2011 ዓ.ም

Ministry
ARCHIVES
2
Finance

## የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት አፈፃፀም
## መመሪያ ቁጥር 2/2011

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስትሩ በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 85(4) ፣ አንቀጽ 99(2) እና በፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 61 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል፡-

ሀ/ "ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች" በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

ለ/ "አዋጅ" ማለት የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

ሐ/ "ደንብ" ማለት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

መ/ "የታክስ ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

ሠ/ "የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት" ማለት በጉምሩክ ኮሚሽን ስር የሚገኝ የገቢ እና ወጪ እቃዎች የሚስተናገዱበት ቅ/ጽ/ቤት ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ለንግድ የሚውሉ እቃዎችን ከውጭ ወደ አገር በሚያስገቡ እና ለአገር ውስጥ ግኘ ከሚፈፀም ክፍያ ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ በተጣለባቸው ሰዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ ስለሚከፈል ግብር

5. <u>ግብር ስለመክፈል</u>

በአዋጁ አንቀጽ 85(1) መሠረት የሠንጠረዥ "ሐ" ግብር ከፋይ ለንግድ የሚውሉ እቃዎችን ወደ አገር ሲያስገባ የእቃዎቹን የጉምሩክ ዋጋ ፣ የመድን አረቦንና የመጓጓዣ ወጪ 3% (ሦስት በመቶ) የንግድ ስራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ይከፍላል፡፡

6. <u>ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች</u>

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች 'ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች' ናቸው፡፡

1. በፌደራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ለመንግስት መ/ቤት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የተካተቱ የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና የክልል መንግስታት መ/ቤቶች የሚስገቧቸው ዕቃዎች፣

2. ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማህበራት የሚያስገቧቸው እቃዎች /ከተቋቋሙበት አላማ ውጭ በንግድ መልክ የሚስገቧቸውን ዕቃዎች አይጨምርም/ ፣

3. በዲፕሎማቲክ እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የሆኑ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖችና የእነዚሁ አባላት የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፡፡

4. የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት የግል መገልገያ እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ወይም ቀረጥና ታክስ ከፍለው እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ግለሰቦች የሚያስገቧቸው እቃዎች፣፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation N 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

5. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 2ተኛ መደብ (ለ) ተጠቃሚ ሆነው እቃዎችን የሚያስገቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣

6. በፌዴራልና በክልል ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት /Tax Holiday/ የተፈቀደላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች በእሮይታው ጊዜ ውስጥ የሚያስገቧቸው እቃዎች፣

7. የአምራችነት ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለሚያመርቷቸው ዕቃዎች በግብአትነት የሚጠቀሙባቸው ጥሬ ዕቃዎች እና ለካፒታል ዕቃዎች የሚያገለግሉ መለዋወጫዎች፣

8. ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ወይም ለማስፋፋት ወይም ለሃይል ማመንጫ ወይም የመገናኛ አገልግሎት ለመዘርጋት ወዘተ ወደ አገር የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል የካፒታል ዕቃዎች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቀረበ፣

9. የንግድ ትርኢት ለመሳተፍ የሚመጡ የውጪ አገር ድርጅቶች ምርታቸውን ለማስተዋወቅ ወደ አገር ውስጥ ይዘውት የሚገቡት እቃ፣

10. በማዕድን እንዲሁም በፔትሮሊየም ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ለነዚህ ስራዎች አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስገቧቸው እቃዎች፣

11. ለሰብዓዊ እርዳታ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች፣

## 7. ወደ አገር ከሚገቡ ለንግድ ከሚውሉ ዕቃዎች የቅድሚያ ግብር ስለመሰብሰብ

1. ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ የቅድሚያ ግብር የሚከፈለው በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ይሆናል፡፡

2. የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ለንግድ ከሚውሉ ዕቃዎች የቅድሚያ ግብር ሲሰበስቡ የግብር ከፋዩን ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመጠቀም መመዝገብና ሂሳቡን በዚሁ መሠረት መያዝ አለባቸው፡፡

3. የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የሰበሰቡት የቅድሚያ ግብር የገቢዎች ሚኒስቴር በሚዘረጋው ስርዓት መሰረት ለገቢው ባለቤት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የሰነዶችና ይከመጋቤት ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሦስት

## <u>በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት</u>

### 8. <u>ግብር ቀንሰው የሚያስቀሩ ሰዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 92 መሰረት በግዥ ወቅት ከሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው

1. በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፡- የአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የሽርክና ማህበር፣ የህብረት ስራ ማህበር፣ ......ወዘተ፣

2. የመንግስት መ/ቤቶች፡- በፌደራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ለመንግስት መ/ቤቶች በተሠጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወይም በተቋቋመበት ሕግ የመንግሥት መ/ቤት የተባሉ የፌዴራል ፣ የክልል ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት መ/ቤቶች፣

3. ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፡- ለትርፍ ላልሆነ ለተለያዩ ዓላማዎች የተቋቋሙ ማህበራትና የሃይማኖት ድርጅቶች፣

4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡- በሲቪክ ማህበራት አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች" ወይም "የኢትዮጵያ ማኅበሮች" ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተመሳሳይ ድርጅቶች፣

5. የገቢዎች ሚኒስቴር በአዋጁ አንቀጽ 92(1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ የተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች፣

6. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በምርት ገበያው አማካኝነት ከሚከናወን ግብይት ጋር በተያያዘ ገዥውን በመወከል የሚፈፅመው ግብይት፣

### 9. <u>ግብር ቀንሶ ለሚያስቀር ሰው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት</u>

1. ከተከፋይ ሂሣቦች ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሰዎች ባለስልጣኑ ለዚሁ አላማ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2. ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የተጣለበት ሰው በባለስልጣኑ ሲመዘገብ ወይም ባለስልጣኑ እንዲመዘግበው በማመልከቻ በመጠየቅ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የተጣለበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት መያዝ አለበት። ይሁን እንጂ በማናቸውም ምክንያት የምስክር ወረቀቱን ሳይዝ የዘገየ ቢሆንም አዋጁ በሚያዘው መሠረት ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

## 10. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት የክፍያ መጠን እና የግብር መጣኔ

1/ በአዋጁ አንቀፅ 92 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 2% (ሁለት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡፡

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አሥር ሺ.ህ ብር) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ለሚፈፀም ክፍያ ፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት ውል ከብር 3,000 (ሦስት ሺ.ህ ብር) በላይ ለሚፈፀም ክፍያ፤

2. በዕቃና አገልግሎት ግዥ ውል መሠረት ከሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ /Advance payment/ ላይ የቅድመ ግብር ክፍያ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

3. በአንድ ውል ውስጥ የተመለከተው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን በተለያየ ጊዜያት ተከፋፍሎ ክፍያ የሚፈጸም ሲሆን ለቅድመ ግብር ክፍያ መሰረት የሚሆነው አጠቃላይ በውሉ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 92 (4) እና በደንቡ አንቀጽ 63 መሰረት ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን (እና የፀና የንግድ ስራ ፈቃዱን (ሁለቱንም)) ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ገዥ ሲያቀርብ ካልቻለ ገዥ ለአቅራቢው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ግብር ተቀናሽ ማድረግ አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ቢኖርም የቤት ኪራይ አገልግሎት እና ባለስልጣኑ ባወጣው የታክስ ደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሰረት በግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ መጠቀም ከሚቻልባቸው ግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው 2 በመቶ ቅድመ ግብር ብቻ ነው፡፡

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተቀናሽ የሚደረገው 2% (ሁለት በመቶ) እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተቀናሽ የሚደረገው 30 በመቶ ግብር የሚሰላበት የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የክፍያ መጠን በግብይቱ ላይ የሚከፈሉ የመንግስት ታክሶችን (እንደየተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ የመሳሰሉትን) እና በሻጭ ገቢ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎችን ሳይጨምር ነው፡፡

7. ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ለጥገና እና/ወይም ዕድሳት የሚፈጸም ክፍያ መጠን

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

ሀ) የጥገና እና/ወይም ዕድሳት አገልግሎት ሰጪዎች ከአገልግሎት ገዢ ጋር ለጥገና እና/ወይም ዕድሳት በሚያደርጉት ውል መለዋወጫ ዕቃዎችን አገልግሎት ሰጪ በደረሰኝ ገዝቶ ሲያቀርብ ገዢ ገንዘቡን እንደሚተካለት የተስማሙ እንደሆነ አገልግሎት ሰጪው ለመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ከሚፈጽመው ክፍያ ላይ በአዋጁ መሠረት ግብር ተቀናሽ አድርጐ ገቢ የማድረጉ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አገልግሎት ሰጪው ለመለዋወጫ ግዥ ያወጣው ገንዘብ በደረሰኙ መሠረት በገዢው ሲተካለት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ 2% (ሁለት በመቶ) ግብር ተቀናሽ የማይደረግበት ሲሆን ግብር ተቀናሽ የሚደረገው ከብር 3,000 (ሶስት ሺ.ህ ብር) በላይ በተከፈለ የአገልግሎት ዋጋ ላይ ብቻ ነው፡፡

ለ) አገልግሎት ሰጪው ራሱ አገልግሎቱን ከመለዋወጫ ዕቃው ጋር በአንድነት የሚያቀርብና ለዚሁ ጠቅላላ ዋጋ የሚከፈለው በሚሆንበት ጊዜ አገልግሎት ሰጪው ከሚያገኘው ጠቅላላ ተከፋይ ሂሣብ ላይ ክፍያውን የፈፀመው ገዢ 2% (ሁለት በመቶ) ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ይኸውም ለዕቃ አቅርቦት ከብር 10,000 (አሥር ሺ. ብር) እና ለአገልግሎት ሲሆን ከብር 3,000 (ሶስት ሺ.ህ ብር) በላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ የመለዋወጫ ዕቃና የአገልግሎት ዋጋውን መለየት አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ ግን አቅርቦቱ ሙሉ በሙሉ የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

ሐ) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የጥገናና እድሳት አገልግሎት ማለት የተሽከርካሪ፣ የተለያዩ ማሽነሪዎች (ሎደር፣ ግሬደር፣ የፋብሪካ ማሽኖች የመሳሰሉት) እና የመሳሪያዎች ጥገናና እድሳትን ይጨምራል፡፡

8. የኮንስትራክሽን አገልግሎት ግዥን በሚመለከት ለኮንስትራክሽኑ ስራ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ኮንትራክተሩ የሚያቀርብ በሚሆንበት ውል መሠረት ለኮንትራክተሩ ከሚፈጸም ክፍያ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረገው እንደ ኮንስትራክሽን ስራው አይነት ከጠቅላላው ክፍያ ቀጥሎ የተመለከተው መቶኛ ብቻ ተወስዶ ይሆናል፡፡

- የህንጻ ግንባታ ............................................... 45
- የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ሲቪል ስራ ......................... 50
- የመንገድ ግንባታ
  - ለጠጠር መንገድ ............................................ 72
  - ለአስፋልት መንገድ
    - ለአስፋልት ኮክሪት (Gravel Asphalt Concrete) .. 65
    - በድርብ ለሚሠራ አስፋልት (Gravel Double Surface Treatment) ............................ 60
    - ለመንገድማሻሻያ (Rehabilitation) ............... 40
  - ድልድይ ስራ ................................................ 55

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

9. አንድ ግብይት የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ በውስጡ ያካተተ እንደሆነ በግብይቱ ላይ ለየብቻ የዕቃ እና የአገልግሎት ቅድመ ግብር ሊያዝ የሚገባው ሲሆን ከግብይቱ ባህሪ የተነሳ የእቃ እና የአገልግሎት ግዥ ብሎ ለመለየት የሚያስቸግር ሲሆን ግብይቱ እንደአገልግሎት ግዥ ይቆጠራል፡፡

10. በሠንጠረዥ መ ገቢዎች ላይ የሚከፈለው ግብር የመጨረሻ ግብር በመሆኑ በዚህ ክፍያ ላይ የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 11. ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የማይመለከታቸው ሰዎች

የሚከተሉት በግዢ ወቅት ከሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የለባቸውም፡፡

1. ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች
2. ላኪዎች/ ወደ ውጭ ለሚልኳቸው ምርቶች በግብዓትነት ለሚያገለግሉ እቃዎች ብቻ/
3. በዲፕሎማቲክ እና አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት የተቋቋሙ ድርጅቶች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ኮንሱላር ሚሲዮኖች ፣ ኤምባሲዎች ፣ የተባባሩት መንግስታት ድርጅት አካላት እና የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ተመሳሳይ አካላት፣
4. የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ቅድመ ግብር የመያዝ ግዴታ ከተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች ውጪ ያሉ ግለሰብ ግብር ከፋዮች፣

## 12. ግብር ቀንሶ የመያዝ ሥርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸው ግብይቶች

1. ግብር ቀንሶ የመያዝ ስርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸው የዕቃ እና የአገልግሎት ግዢዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

   ሀ) የሰው ወይም የእንስሳት ህክምና አገልግሎት

   ለ) የመደበኛ ትምህርት አገልግሎት (ሥልጠናን አይጨምርም)

   ሐ) የፋይናንስ አገልግሎት/ ባንክ የደንበኞቹን ንብረት ሲሸጥ የሚቀበለውን ክፍያ አይጨምርም

   መ) የኤሌክትሪክ አገልግሎት

   ሠ) የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የመዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance
ARCHIVES
2

ረ) የየብስ፣የአየር፣ የባህር እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት/ኪራይን አይጨምርም

ሰ) የውሃ አገልግሎት /ታሽጎ የሚሸጥ ውሃን አይጨምርም/

ሸ) ከገቢ ግብር ነፃ መብት (Tax Holiday) የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ከግብር ነፃ በሆኑበት ጊዜ ውስጥ የሚሠጡት አገልግሎት ወይም የሚያቀርቡት ዕቃ

ቀ) በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግባቸው የሰንጠረዥ "መ" ገቢዎች፣

በ) የነዳጅ አቅርቦት /ቅባት እና ዘይቶችን አይጨምርም/

ተ) በፌደራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ለመንግስት መ/ቤት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱወይም በተቋቋመበት ሕግ የመንግሥት መ/ቤት የተባሉ የፌዴራል፣ የክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት መ/ቤቶች የሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች

ቸ) ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት የሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች/ከተቋቋሙበት አላማ ውጪ በንግድ መልክ የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች አይጨምርም

ኀ) በዲፕሎማቲክና ሌሎች ዓለምአቀፍ ስምምነቶች መሠረት ለተቋቋሙ የአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱላር ሚስዮኖችና ኤምባሲዎች እና የተባበሩት መንግስታት አካላት የሚፈጸም ክፍያ

ነ) በገቢ ግብር ህግ መሰረት ከግብር ነጻ ከሆነ ገቢ

ኘ) ከመንግሥት በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ ድርጅቶች፣

አ) የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸምለት ክፍያ

ከ) የፋብሪካ ምርት ያልሆነ የአርብቶ አደር እና የአርሶ አደር የግብርና እና የእንስሳት ውጤት እንዲሁም ከእንስሳት የሚገኝ አገልግሎት

ኸ) የመኖሪያ ቤት ሽያጭ

ወ) በሰው ጉልበት የሚከናወን ዕቃ የመጫንና የማውረድ አገልግሎት፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ... ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

ዐ) ቅይጥ ግብይት/ በአንድ ግብይት ውስጥ ቅድመ ግብር የሚመለከተው እና የማይመለከተው ግኝ

ዘ) በማቋቋሚያ ህጋቸው ከገቢ ግብር ነጻ የሆኑ ተቋማት

2. በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሚኒስትሩ ለሌሎች እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ግዢ የሚፈጸም ክፍያ የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት ተፈጻሚ እንዳይደረግበት ሊወስን ይችላል፡፡

## 13. <u>ግብሩን ቀንሶ እንዲያስቀር ግዴታ የተጣለበት ሰው ተግባርና ኃላፊነት</u>

ግብር ቀንሶ እንዲስቀር ግዴታ የተጣለበት ሰው ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶች አሉበት፤

1. በአገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ በወሩ ውስጥ ቀንሶ ቀሪ ያደረገውን አጠቃላይ ግብር ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ፣

2. ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ክፍያ የተፈፀመለትን እና ግብር የተቀነሰበትን የእያንዳንዱን ሰው ወይም ድርጅት ስም፤የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/፤ በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር፣ ተቀናሽ ተደርጎ የቀረውን ግብር እና በእያንዳንዱ ሰው ስም ለባለስልጣኑ ገቢ የተደረገውን ሂሳብ የሚያሳይ ዝርዝር ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ ፣

3. በእያንዳንዱ የግብር ዘመን የተፈፀሙ ክፍያዎችና ከነዚህ ክፍያዎች ተቀንሶ የቀረውን ግብር የሚያሣይ የሂሣብ ሰነዶችን የመያዝና ባለስልጣኑ ምርመራ እንዲደረግባቸው ሲጠይቅ የማቅረብ ፣

4. የተፈፀሙ ክፍያዎችና ከነዚህ ክፍያዎች ተቀንሶ ስለቀረው ግብር የሚያሣዩ የሂሣብ ሰነዶች በንግድ ህግ ለተወሰነው የሰነድ መያዣ ጊዜ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ለባለስልጣኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለ5 አመታት፣ ከሁለቱ ረዥም ለሆነው ጊዜ ማቆየት ፣

5. ከላይ የተገለፁትን ሠነዶች ኮፒ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ቅፅና ሁኔታ እንዲሁም በሚወስነው የጊዜ ልዩነት እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ማቅረብ ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

6. ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው በክፍያ ወቅት ግብር ቀንሶ ሲያስቀር የግብር ከፋዩን ስም ፣አድራሻና የግብር ከፋዩን መለያ ቁጥር በመጠቀም መመዝገብ እና ሂሳቡን በዚሁ መሰረት መያዝ ፣

7. ግብር ለተቀነሰበት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ መስጠት፡፡

## ክፍል አራት

## የሂሳብ አመዘጋገብ ማካካሻ እና የተመላሽ አፈጻጸም

### 14. የቅድመ ግብር ክፍያ አመዘጋገብ፣ሪፖርት አቀራረብና የገቢ ማስተላለፍ

1. በታክስ ባለስልጣናት ስለሚደረግ የቅድመ ግብር ክፍያ ሂሳብ አመዘጋገብ

ሀ) ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተቀነሰ ታክስ የንግድ ትርፍ ግብር ወይም የቤት ኪራይ ገቢ ግብር አካል በመሆኑ የታክስ ባለስልጣናት የራሳቸውን ድርሻ ሲሰበስቡ በተለመደው የቀጥታ ታክስ ገቢ እንደ አግባብነቱ በ1102 ወይም በ1104/1103 በመደበኛ ገቢነት ይመዘግባሉ፡፡

ለ) የታክስ ባለስልጣናት ከራሳቸው ህጋዊ ገቢ ውጭ የሌሎች ታክስ ባለስልጣናትን ድርሻ የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ሲያጋጥም በአደራ ሂሳብ ቁጥር 5026 መመዝገብ አለባቸው፡፡

ሐ) የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ ባለስልጣናት ከሚሰበስብ የቅድመ ግብር ክፍያ ጋር በተያያዘ ግብሩን ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው እና ገቢውን የሚሰበስበው የታክስ ባለሥልጣን ሂሳቡን የሚመዘገብበትን፣ ገቢው እና ከገቢው ጋር የተያያዘ አግባብነት ያለው መረጃ የገቢው ባለቤት ለሆነው የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለሥልጣን የሚተላለፍበትን፣ ሪፖርት የሚዘጋጅበትና ለሚመለከታቸው አካላት የሚቀርብበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

2. ግብር ቀንሰው የሚያስቀሩና ግብር የሚቀነስባቸው ሰዎች ሂሣብ አመዘጋገብ

ሀ) ማንኛውም በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ዕቃም ሆነ አገልግሎት ሲገዛ እንዲሁም ሻጩ ዕቃም ሆነ አገልግሎት ሲያቀርብ አጠቃላይ የግዥውን ወይም የሽያጩን ሙሉ ዋጋ በሂሳብ መዝገብ መመዝገብ አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የሰነዶች መዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
ARCHIVES 2

ለ) ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የሚገዛው ሰው ወይም ድርጅት ሙሉ ክፍያውን እንደወጪ በመመዝገብ 2% /ሁለት በመቶ/ ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ግብሩን በደረሰኝ ገቢ በማድረግ ይመዘግባል፡፡ አመዘጋገቡም፡-

- ግዥ /ተከፋይ ሂሣብ /100%/ ............................... ዴቢት
- ጥሬ ገንዘብ /cash (98%) ............................... ክሬዲት
- የቅድሚያ ግብር ክፍያ Withholding tax payable (2%) .... ክሬዲት

በማድረግ ይሆናል፡፡

ሐ) የዕቃው ወይም የአገልግሎት አቅራቢም ሙሉ ሂሣቡን ተቀብያለሁ ሲል ደረሰኝ በመስጠት ለ2% /ሁለት በመቶ/ ከተከፋይ ሂሣብ የሚቀነስ ቅድሚያ ግብር ከፈልኩ በማለት ገዥው በሚሰጠው ደረሰኝ መሠረት በቅድሚያ ግብር ክፍያ ይዞ በሂሣብ መዝገቡ ያሰፍራል፡፡

በዚህም መሰረት ፡-

- ጥሬ ገንዘብ (98%)......................................... ዴቢት
- የቅድሚያ ግብር ክፍያ /pre paid tax/ (2%)......... ዴቢት
- ሽያጭ /ተሰብሳቢ ሂሣብ (100%) ........................ ክሬዲት

በማድረግ መመዝገብ አለበት፡፡

መ) ገገርው በተከፋይ የተመዘገበውን የቅድሚያ ግብር ለግብር ባለስልጣን ገቢ ሲያደርግ "የቅድሚያ ግብር ክፍያ" ሂሣብ ዴቢት ጥሬ ገንዘብ ወይም ባንክን ደግሞ ክሬዲት በማድረግ ሂሳቡን ያካክሳል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ሻጩ የዓመቱን ሂሳብ ዘግቶ የሚፈለግበትን የንግድ ትርፍ ግብር /ክሬዲት/ ሲከፍል በቅድሚያ ግብር ክፍያ (Advance ወይም prepaid tax) ላይ ከሚታየው ሂሳብ /ዴቢት/ ላይ በማቀናነስ ልዩነቱን ይከፍላል፡፡

## 15. ተቀንሶ ገቢ የተደረገ ግብር ስለማካካስ እና ተመላሽ አፈጻጸም

1. ግብር ከፋዩ የግብር ዘመኑ ካለፈ በኃላ ቀደም ሲል በነበሩት የግብር ዘመናት ያልተቀነሰ ቅድመ ግብር ክፍያ የከፈለ እንደሆነ እንዲሁም ቅድመ ግብሩ ከተከፈለ በኂላ የተገዛው ዕቃ ተመላሽ የተደረገ ወይም የኪራይ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት ውሉ የተቋረጠ እንደሆነ፣ በግዥው ወቅት የተከፈለው ቅድመ ግብር በተከፈለበት ግብር ዘመን ለሚፈለግበት የኪራይ ገቢ ግብር ወይም የንግድ ትርፍ ግብር ማካካሻ ይውላል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

2. በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 49 እና 50 መሰረት ግብር ከፋዩ በብልጫ የተከፈለ የቅድሚያ ግብር ክፍያ ተመላሽ ሲጠይቅ ባለሥልጣኑ በግብር ከፋዩ የቀረበው የሂሳብ መግለጫ ዕውቅና በተሰጠው የውጭ ኦዲተር የተመረመረ መሆኑን በማጣራት እና ግብር ከፋዩ ያቀረባቸው የይካካስልኝ ወይም የይመለስልኝ ጥያቄ በደጋፊ ሰነድ የተደገፈና የቅድመ ታክስ ክፍያው ዝርዝር መረጃ ለምሳሌ መቼ ተቀናሽ እንደተደረገ፣ ከየትኛው ሽያጭና ምን ያህል እንደተቀነሰ እንዲሁም እንዲመለስለት ያቀረበውን የቅድሚያ ግብር ክፍያ በዕቃ ግዥ ዋጋ ውስጥ ያለማካተቱን ወይም በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዙን የመሳሳሉትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3. የሂሳብ መዝገብ ለማይዝ ወይም የሂሳብ መዝገቡ ውድቅ ለሆነ ግብር ከፋይ ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ፣ በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር እና በግብር ዓመቱ ተከፋፍሎ ለባለስልጣኑ ገቢ የተደረገ ግብር በሚቀርበው ማስረጃ መሠረት ይቀነሳል፡፡

4. በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 49 መሰረት ታክስ ከፋዩ በግብር አመቱ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለቀረበት በቅድሚያ ለከፈለው ግብር ማካካሻ ለማግኘት ባለሥልጣኑ በሚወስነው አኳኋን ግብሩን ያቀናነሰበትን የደረሰኝ እና የዲክላራሲዮን ዝርዝር ሠንጠረዥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 50 መሰረት ታክስ ከፋዩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በቅድሚያ የከፈለው ግብር ሊከፍል ከሚገባው በላይ መሆኑ ተረጋግጦ በብልጫ የከፈለው ገንዘብ በሌሎች የታክስ ሕጎች መሰረት ለሚፈለግበት ዕዳ ተካክሶ ተራፊው ገንዘብ እንዲመለስለት ከተወሰነ ተመላሽ የሚፈጸመው ለዚሁ አላማ ተብሎ ከተያዘ በጀት ላይ ይሆናል፡፡

## 16. <u>የክልል/የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣናት የስራ ኃላፊነት</u>

የክልል፣ የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለሥልጣናት፣

1. የታክስ ግዴታቸውን በክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣናት በኩል የሚወጡ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች እና ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ተቀናሽ እንዲያደርጉ ሕጉ ኃላፊነት ለሰጣቸው አካላት የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡

2. ግብር ቀንሰው ገቢ የማድረግ ግዴታ የተጣለባቸው የክልል /የከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች ቀንሰው ያስቀሩትን ግብር የሚያስታውቁበትንና ገቢ የሚያደርጉበትን ቅፅ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው ዓይነት በማሳተም ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

3. ግብር ቀንሰው ገቢ የማድረግ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነሰውን ግብር አስመልክቶ የግብር ከፋዮቹን ማንነት፣ የከፈሉትን የግብር መጠንና የክፍያውን ጊዜ የሚገልጽ መዝገብ ወይም ፎርም እንደአስፈላጊነቱ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው ዓይነት በማሳተም ጥቅም ላይ ያውላሉ፡፡

4. ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ግዴታ የተጣለባቸው በእያንዳንዱ ግብር ቀንሶ በሚያስቀር ሰው ስም ማህደር ይከፍታሉ፡፡

5. ከቅድመ ግብር ክፍያ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችን የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የሚመለከታቸው ሌሎች አካላት በመመካከር መፍትሔ እንዲያገኙ ይደረጋሉ፡፡

6. በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ለግብር ከፋይ ተመላሽ ክፍያ የሚውል በጀት ይይዛሉ፡፡

7. ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ግዴታ የተጣለባቸው አካላት መቼ፣ ከማን፣ እና እንዴት ግብር ቀንሰው በየደረጃው ለሚገኙ የታክስ ባለስልጣናት ገቢ ማድረግ እንደሚገባቸው ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣሉ፡፡

8. የክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣናት ከቅድመ ግብር ክፍያ ሰብስበው ለሌሎች ታክስ ባለስልጣናት ያስተላለፉትን ገንዘብ አስመልክቶ ለገቢዎች ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 17. <u>የገቢዎች ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር፣

1. ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ቀንሶ ያስቀረውን ግብር የሚያስታውቅበትና ገቢ የሚደረግበት፣ የሚመለከታቸው አካላት ስለመቀነሱ እንዲያውቁት የሚደረግበት እና ግብር ከፋዮቹ እነማን መሆናቸውን የሚገልፅ መረጃ የሚመዘግብበት መዝገብ ወይም ፎርም ያዘጋጃል፤

2. ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች የገቢ ግብር አዋጁ በሚያዘው መሠረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር በእያንዳንዱ ግብር ቀንሶ በሚያስቀር ድርጅት/ሰው ስም ማህደር ይከፍታል፡፤

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of Archives Finance

3. በአፈፃፀም በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለሥልጣናት እንዲሁም ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር መፍትሔ ይሰጣል፡፤

4. ለግብር ከፋዮች የተመላሽ ክፍያ የሚውል በጀት ይይዛል፡፡

5. ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ግዴታ የተጣለባቸው አካላት መቼ ከማን እና እንዴት ግብር ቀንሰው ግብር ከፋይ ሆነው ለተመዘገቡባቸው ለታክሱ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ ማድረግ እንደሚገባቸው ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡

6. ከቅድመ ግብር ክፍያ ተሰብስቦ ለክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች ያስተላላፈውን ገንዘብ አስመልክቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 18. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

በገቢዎች ሚኒስቴር ሰኔ 25 ቀን 1995 ዓ.ም በቁጥር 01/አ36/35/4 የተላለፈው የቅድመ ግብር ክፍያን ለማስተዳደር የተዘጋጀው የአፈጻጸም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 19. <u>መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*